# የዓድዋ ድል 107ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል

*በሲያትል የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማሕበር ጋባዥነትና አስተናጋጅነት ለዓድዋ ድል 107ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል በ ዶ/ር ገላውዴዎስ አርኣያ የቀረበውን ንግግር በግዜው ታትሞ ባለመውጣቱ፡ የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (ኣልትተ) የ110ኛ ዓመት በዓል መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ለአንባብያን ያቀርባል።*

---

*ዶ/ር ገላውዴዎስ አርኣያ*

ክቡር እምክቡራን ኢትዮጵያውያን ወገኖች፡

መጀመርያ ይህንን የጀግኖች ቀን፡ የስመጥሩ ኢትዮጵያውያን አርበኞች ዕለት፡ ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ኣህጉር ነጻ ሆና እንድትቀጥል ያደረጋትን ዘመን ለማስታወስ ለተደረግልኝ ጥሪ ምስጋናየ እጅግ የላቀ ነው።

የዓድዋን ድል ጠለቅ ብለን እንድንመረምርና ሰፋ ባለ መልኩ ለማየት በግዜው የነበረውን የዓለም ኣቀፍ የፖለቲካ ሁኔታና የኢትዮጵያም ኣንጻራዊ የፖለቲካ ክስተቶችን ማየት ይኖርብናል።

በመጨረሻው የ19ኛው ክፍለ ዘመን ወይንም ከ1850ዎቹ ጀምሮ ዘመኑ እስከ ተገባደደበት ግዜ ድረስ፡ የኣውሮጳ ኃያላን አፍሪቃን እንደ ቅርጫት የተከፋፈሉበት ግዜ ነበር። አፍሪቃን በቀኝ ግዛት ለመያዝ ቀደም ብለው በ1800ቹ ቢጀምሩትም ቅሉ በቅጡ የአህጉሪቷን መሬት መያዝ የጀመሩት ግን በ19ኛ መቶ ዓመት ኣጋማሽ ማለትም ኣጼ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ግዜ ነው። ይህንን የአፍሪቃ መሬት መንጠቅና ህዝቦቿን በቅኝ ግዛት ለማስተዳደር ይፋ ያደረጉት ግን በ1884-85 እኣኣ በበርሊኑ ጉባዔ ነው። ስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ጀግና፡ የአፍሪቃ ታላቂ ጀነራል ብለው የተሰየሙት ራስ አሉላ አባ ነጋ ከጣልያኖቹ ጋር በሰሓቲ፡ ምጽዋዕ አከባቢ ፍልምያ የያዙበት ግዜ ነበር።

የበርሊኑ ጉባኤ ከተገባደደ በኋላ በ1887 ራስ አሉላ በመሩት የኢትዮጵያ ሠራዊት የጣልያንን ሠራዊት ዶግዓሊ (ምጽዋዕ ኣጠገብ) ላይ ክፉኛ በመምታት ድል ይቀዳጃል። ታድያ ምን ይሁን፡ ዘመኑ የፈተና ዘመን ነውና ኣጼ የውሃንስ የኢትዮጵያን ነጻነት ለማስጠበቅ ኣንዴ ከግብጾች ቀጥለውም ከጣልያኖች ከ1875 እስከ 1887 ሳያቋርጡ ጦርነቶች ስያካሂዱ ከቆዩ በኋላ፡ በማርች 1889 ዓ.ም. መተማ ውስጥ ከድርቡሾች ጋር በተደረገው ጦርነት ይቆስሉና፡ በማግስቱ ይሞታሉ። ወደ ቀይ ባሕር አፈግፍጎ የነበረውን የጣልያን ሠራዊት በጀነራል ባልዲሰራ መሪነት በዚሁ ወር አስመራ ይገባል። የራስ አሉላ ግዛት የነበረውን ምድረ ባሕርም 'ኤርትራ' ብለው ይሰይሙና የመጀመርያው የጣልያን ቅኝ ግዛት በአፍሪቃ ይመሰርታሉ።

አጼ የውሃንስ በሞቱ በሁለት ወራቸው አጼ ምንሊክ በትረ መንግስቱን በመጨበጥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይሆናሉ። በመይ 2 1889 ደግሞ ጣልያንና ኢትዮጵያ የውጫሌን ውል ይፈራረማሉ።

በውጫሌው ውል ኣንቀጽ 3 መሰረት የኤርትራን መልክኣ ምድር ስፋት ምጽዋዕ-ኣስመራ-ሰገነይቲ ብቻ ያካተተ ነበር። ጣልያኖች ግን ውሉን በመጣስ የቅኝ ግዛታቸውን በማስፋት ኣከለጉዛይ፣ ሠራየ፣ በከፊልም የምዕራባዊ ቆላን መቆጣጠርና መያዝ ጀመሩ። ይህንን የጣልያኖች ድርጊት ለኢትዮጵያና ኢጣልያ ያለመጣጣም መንስኤ ከመሆኑም በላይ የፖለቲካ ግጭት ሊፈጥር የቻለው ግን በውጫሌው ውል 17ኛው ዓንቀጽ ትርጉምና ፍቺ በሁለት ኣገሮች የተለያዩ ኣመለካከትና ኣቋሞች እንዲኖሩዋቸው ማድረጉ ነው።

ዓንቀጽ 17 ከሞላ ጎደል እንዲህ ይል ነበር፦

*የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሌሎች ኃያላንና መንግስታት በምያደርገው ማንኛውም ግንኙነት በጣልያን መንግስት ኣመካኝነት መሆኑን ያረጋግጣል ወይም ይስማማል።*

“ይስማማል” የሚለው ቃል በጣልያኑ ትርጓሜ ‘consente’ የሚል ሆኖ የተሰጠው ፍቺ ግን የኢትዮጵያ መንግስት የጣልያንን ፍላጎት ማሟላት እንዳለበት ነው። ባማርኛው ትርጓሜው ግን ‘consente’ ሳይሆን ‘supporte’ ለሚለው ቃል ‘ኣጋዥነት’ ብሎ ነው ያሰፈረው። ስለሆነም ኢትዮጵያ የጣልያንን ፍላጎት ለማሟላት ሳይሆን በጣልያን ኣጋዥነት ግን ከኣውሮጳ መንግሥታት ጋር ግንኙት መመስረት እነደምትችል ነው።

ከዚህ የባሰ ግን ጣልያኖች ዓንቀጽ 17ትን ሰፋ ባለ መልኩ ሲተረጉሙት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛት ስልጣን ሊኖራት እንደሚችል ነው የገለጹት። ይኸንን ኣገላለጽ የኢትዮጵያን መንግስት አስቆጥቶታል። ኣጼ ምንሊክ ደግሞ ብልህና ኣስተዋይ መሪ ስለነበሩ በውሉ መሰረት ሊሰጣቸው የነበረውን ሁለት ምልዮን የብረት ካርትርጅ በትራቨርሲ የተባለውን የጣልያን ተወካይ በፌብርዋሪ መጀመርያ ከተረከቡና እጃቸው ውስጥ መግባቱን ካረጋገጡ በኋላ፣ በዚሁ ወር መጨረሻ ላይ፣ ማለትም በፌብርዋሪ 27 1893 የውጫሌ ውል ውድቅ መሆኑን በይፋ ለዓለም ሕዝብ ኣስታወቁ።

ጣልያኖች የኢትዮጵያን መንግስት ኣቋምና ውጫሌ ውል መፍረሱን ካረጋገጡ በኋላ የሮም መንግስት፣ በኣንድ በኩል የማስፋፋት ፍላጎትን ትቶ በውሉ መሰረት ወደ መጀመርያው ድንበር ምጽዋዕ-አስመራ-ሰገነይቲ እንደሚመለስና በዚሁም እነደሚጸና ሲገልጽ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመይ 5 1894 ሮም ውስጥ ከእንግሊዞች ባደረገው ስምምነት መሰረት የኢትዮጵያን ካርታ ሙሉ በሙሉ በግዜው ከወጣው የዓለም ካርታ ፍቀው ማውጣታቸው ነው።

በተጨማሪም በዲሰምበር 15፣ 1894 ጣልያኖች በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ-ሃገር በትግራይ ላይ የጥቃት ዘመቻቸውን ሰነዘሩ። ራስ መንገሻ ዮውሃንስ ደግሞ በበለሳና

በኣከለጉዛይ የሰፈረውን የጣልያን ሰራዊት እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና ለማጥቃት ክተት የተሰኘውን የራሳቸው ሠራዊት በማሰማራት በማርች 1895 ዘመቻ ጀመሩ። ዳሩ ግን የክተት ሠራዊት ከሌላው የኢትዮጵያ ሠራዊት እርዳታ ስላላገኘ ጣልያኖች በሦስት ኣቅጣጫ በመግባት የትግራይን መሬት መውረር ጀመሩ።

በጀነራል ባራቴሪ የሚመራ ከቅናፍና (ሠራየ) በመነሳት፡ በጀነራል ቶሰሊ የሚመራውን ያገር ሰዎች (ኤርትራውያን/ጥቁር ሠራዊት) ባታልዮን ይዞ ወደ ማይ መገልታ በመዝለቅ፡ በጀነራል ኣመልዮ የሚመራው ደግሞ ሓውዜንን ለመቆጣጠር መጀመሩ ለትግራይ ሕዝብ መነሳሳት መንስኤ ይሆናል፡

የመጀመርያው የጣልያንና የትግራይ የክተት ሠራዊት ደብሪ ዓላ ላይ ጦርነት ይገጥሙና ጣልያኖች ግዝያዊ ድልን ይቀዳጃሉ፡ ወደ ኣምባ ኣላጄም ይዘልቁና፡ 'የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል' እንዲሉ ትግራይን ግዛታቸው መሆኑን ያስታውቃሉ።

ጣልያኖች ኣምባ ኣላጄን መቆጣጠራቸውን ከተሰማ በኃላ ኣጼ ምንሊክና ሌሎች የኢትዮጵያ መኳንንት የተባበረ ጥቃት ለማካሄድ ሠራዊቶቻቸውን ወደ ኣምባ ኣላጄ ማሰጠጋት ጀመሩ፡ በጣልያን ሠራዊት ላይ ሽብርና ውዥንብር ለመፍጠርም በቅድምያ የስነ-ልቦናዊ ጦርነት (የተዛባ ወሬ በማሰራጨት) ኣካሂደዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጣልያኖች ሳያውቁ ኣጼ ምንሊክና የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ኣምባ ኣላጄ እጅግ በጣም ተጠጉ። ከመንፈቀ-ሌሊት ሦስት ሰዓት በኋላ በዲሰምበር 7 1895 በራስ ኦሌ (ወሌ) የሚመራውን 7000 ሠራዊት የጣልያን ቦታዎችን ማጥቃት ጀመረ። ልክ ከጠዋቱ 9፡45 ደግሞ የራስ መንገሻና ራስ ኣሉላ ሠራዊት የጣልያንን የቀኝ ክንፍ ሠራዊት ስያጠቁ፡ የራስ መኰንንና የራስ ሚካኤል ሠራዊት ደግሞ 'የእንግሊዝ መንገድ' የተሰኘውን (በእንግሊዝና ባጼ ቴዎድሮስ ጦርነት ግዜ የተሰራ) ተቆጣጠሩ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ኣምባ ኣላጄን መቆጣጠር ሲጀምር ጣልያኖች በ12፡40 ከሰዓት በኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ። ነገር ግን የማምለጫ መንገዳቸውን በራስ ኣሉላ ሠራዊት ስለተዘጋ በቀላሉ ማፈግፈግ ኣልቻሉም። በዚሁ በኣምባ ኣላጄ ጦርነት ላይ 500 ኢትዮጵያውያን መስዋእት ሲሆኑ 1300 የጣልያን ወታደሮች ደግሞ ተገድሏል። በጣልያንም በኩል 20 ዝነኛ የሆኑት ባለከፍተኛ መዓርግ መኰንኖች እንደነ ቶሰሊ፡ ስካለ፡ ማንፍረዶ፡ ኣንገራ ተገድሏል።

ከኣምባ ኣላጄ ያመለጡ የጣልያን ወታደሮች ጦርነቱን ኣስመልክቶ እንዲህ ብለዋል፦

"የኢትዮጵያውያን ብዛት እንደ ጉንዳን ነበር፡ መሬትም ሊሸከማቸው የቻለ ኣይመስልም"

የጣልያን ጦር ሠራዊት ዋና ኣዛዥ ባራቴሪም የኢትየጵያ ሠራዊት ድል መቀዳጀቱን ካመነ በኃላ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ "ለቀኝ ግዛታችን ዋነኛ መከላከያ የሆነውን ጠቅላላ የፖለቲካ ግዙፍ መዋቅር ከመሰረቱ ተገርስሶ ወድቋል፡ በመጠኑም

ወደ መሬት ስለወደቀ የጠላትን ቆራጥነት፡ መተማመንና ጥንካሬ እንዲሁም ትምክህተኝነት እንዲጭምር አድርጎታል።”

ከአምባ አላጄ በኋላ ባራቴሪ የጣልያን ሠራዊት ትግራይን ለቆ እንዲወጣና የተቀረውን 2000 ወታደር በጋልያኖ የሚመራ ግን መቐለ ላይ ምሽግ እንድይዝ ትእዛዝ አስተላለፈ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ግን ጣልያኖችን ከኢትዮጵያ መሬት ለማስወጣት ቆርጦ ስለተነሳ ወደ መቐለ አከባቢ አመራ። በዲሰምበር 11 ራስ መኰንን ኢትዮጵያን በመወከል ከጣልያኖች ጋር ድርድር ያዙ። ሆኖም ግን ባ19ነኛው ቀን በዚሁ ወር የኢትዮጵያ ሠራዊት መቐለ እንዳ እየሱስ ላይ የመሸገውን የጣልያን ሠራዊት ከመክበቡም በላይ ከዓዲግራት ሊኖረው የሚችለውን ግንኙነትም ቆርጦታል።

በዲሰምበር 20 ለፍተናንት ሞልቴዶ የመጀመርያው የመድፍ ተኵስ ይከፍታል፡ በሦስተኛው ቀን ማለትም በዲሰምበር 23 የመቐለ ጦርነት ይጀመራል። የተፋፋመ ጦርነት መካሄድ የጀመረው ግን በጃንዋሪ 7 1896 (በኢትዮጵያ ልደተ-ክርስቶስ -ገና- በዓል) ነው። እስከ 20ኛው የዚሁ ወርም ጦርነቱ ቀጥሏል።

የመቐለ ጦርነት በመካሄድ ላይ እንዳለ ራስ መኰንን ለጋልያኖ ዳብዳቤ ይልካሉ፡ መልእክቱም ከሞላ ጎደል እንዲህ ይላል፦

“እኔ በያዝከው ትንሽ ምሽግ ላይ ጦርነት ለመክፈት አልመጣሁም፡ እኛ ብዙ ነን፡ ለጠመንጃችሁም ፍራቻ የለንም፡ አምባ አላጄና የቶሴሊ ፍጻሜን አስታውስ፡ ምሽጉ ለኔ ለቀህ ውጣ፡ ያለምክንያትም ደም እንድናፈስ አታስገድደን። እስከ ምጽዋዕ ሸኚ እንዲኖርህና ጓዝህንም እዛው ድረስ እንደሚላክ ቃል እገባልሃለሁ፡”

በመቐለ ጦርነት ላይ ኢትዮጵያውያን የበላይነተን ያሳዩት በሦስት ረገድ ነው፦

1) የሰራዊት ብዛት፡ ጀግንነትና ቆራጥነት
2) የውሃ መስመሮችና የመገናኛ አውታሮችን መቆጣጠር
3) የመድፍ ተኵስ ርዝመት የኢትዮጵያውያን 4500 ሜትር ሲሆን የጣልያኖች ግን 3850 ሜትር በቻ ለመኖሩ።

ጣልያኖች የራስ መኰንን ትእዛዝና ፍላጎት ስላላሟሉ ከጃንዋሪ 8 ጀምሮ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከከበባቸው በኋላ በጃንዋሪ 9፡ 10ና፡ 11 ያለማቋረጥ ጥቃትን ሰንዝሮባቸዋል። በዚሁ ግዜ የኢትዮጵያ ሠራዊት የተጠቀመባቸውን የጦር መሳርያዎች በአምባ አላጄ ጦር ግዜ ከቶሰሊ የተነጠቁ ናቸው።

በ19ኛው ጃንዋሪ፡ ጣልያኖች መቸነፋቸውን ከተገነዘቡ በኋላ ነጭ ባንዴራ ማውለብለብ ጀመሩ። ነገር ግን ሁለት ግዜ በተከታታይ በጀግኖች የኢትዮጵያ አርበኞች ቢቸነፉም ቅሉ “በኋላቀር ወይም ባርባርያን” (በነሱ አንደበት) የኢትዮጵያ ሕዘብ ለመቸነፋቸው ልያምኑ አልቻሉም። እንድያውም በርክሊ የተባለው የዘመኑ

ጸሓፊ ‘የዓድዋ ዘመቻና የምንሊክ መነሳሳት’ በሚል መጽሓፉ የጣልያኖች ትዕቢት በእንዲህ መልክ ያሰቀምጠዋል፦

“እነኚ ኋላቀሮች በሳይንሳዊ መንገድ ለታነጸው ምሽጋችንና ጠመንጃቻችን በግምት ሳያሰገቡ ገፍትረው ለመግባት ለግማሽ ሰዓት ያህል ጽኑ ጥቃት ሰንዝረውብናል”

የኢትዮጵያ ጀግኖች ግን፡ ‘የናቁት ያስረግዛል’ እንደሚባለው ሁሉ፡ በሳይንሳዊ መንገድ የታነጸውን የጣልያን ምሽግ እንክትክቱን ኣወጡት። ጣልያኖችም ዳግማዊ ችንፈት ደረሰባቸው። ከተቸነፉም በኋላ ኣጼ ምንሊክ ለጣልያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ ደብዳቤ ጽፈዋል፦

“የክርስትያን እምነታችንን ግብረገብነት ለማሳየት በእንዳ እየሱስ ምሽግ ውስጥ ተጠምተው፡ ተዳክመው፡ ተከበውና በጫማችን ስር ላይ ተጨፍልቀው የነበሩትን ሠራዊታችሁ ጓዛቸውን ጠቅልለውና ጤንነታቸው ተጠብቆ በራስ መኰንን ኣጀቢነት እንዲወጡ ፈቅደንላቸዋል”

ከዚሁ ከሁለተኛው ጣልያን ችንፈት በፊት ደግሞ ራስ መኰንን ለጋልያኖ ኣስተማማኝ ማፈግፈግ እንደሚደረግለት በተቀያየሩት ደብዳቤዎች በግልጽ ኣስፍረውት ነበር። የመኰንንና ጋልያኖ የደብዳቤ ልውውጥ በከፊል እነደሚከተለው ነበር፦

Ras Mekonnen’s letter to Galliano:

Come stai Io sto bene grazie a Dio, I tuoi soldati stanno bene. A nome del mio imperatore to prego di lasciar libero questo terrenoi altrimenti mi costrigni a fare la Guerra. Sono molto dolente di dover spargere sangue cristiano. Ti prego precio d’andartene coi tuo soldati. Tuo amico Maconnen.

Galliano’s letter to Mekonnen:

Come stai? Io sto bene grazie a Dio. I miei soldati stanno benissimo. Come spero sia altrettanto dei tuoi. Il mio Re ha ordinato che io stia qui io non mouvero. Fa oure quello che credi e tio avverto che qui con me ho degli ottimi fucili e dei buonissimi cannoni. Tuo amico Galliano.

የራስ መኰንንና የጋልያኖ ከላይ በጣልያኝና የሰፈረውን ከሞላ ጎደል የሚከተለውን መልእክትና ይዘት ነበራቸው፦

የራስ መኰንን ደብዳቤ ወደ ጋልያኖ፡

እነዴት ነህ፡ እኔ ደህና ነኝ እግዚኣብሔር ይመስገን፡ ወታደሮችህ ደህና ናቸው ወይ፡ የኔ ንጉሠ ነገሥት ቦታውን ለቀህ ከሄድክ ባንተ ላይ ጦርነት ከማካሄድ እንድቆጠብ ኣዘውኛል። የክርስትያን ደም ላለማፍሰስ ጥንቃቄ እናደርጋለን፡

ጓደኛህ መኰንን

የጋልያኖ ደብዳቤ ወደ መኰንን፡

እነዴት ነህ፡ እኔ ደህና ነኝ እግዚኣብሔር ይመስገን፡ የኔ ወታደሮች ደህና ናቸው፡ ያንተም እነደዚሁ ደህና ይሆኑ ዘንድ እመኛለሁ። የኔ ነጉሥ በቦታው እንድቆይና ለቅቄ እናዳልሄድ ኣዞኛል።

ጓደኛህ ጋልያኖ

ጋልያኖ ግን በቃሉ የማይጸናበት ሁኔታ ስለተፈጠረ፡ በጃንዋሪ 24 1896 የጣልያን ወታደሮች ከመቐለ ጠቅልለው በመውጣት ዕዳጋ ሓሙስ ላይ ከነበሩት ሌሎች ሰራዊቶቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። ነገር ግን ኣሁንም ቢሆን ከችንፈታቸውና ከውርደታቸው ኣልተማሩም። እንድያውም ጀነራል ባራቴሪና ባልደረቦቹ ትዕቢት ወጥሯቸው ስለነበር እንዲህ ብለው ደነፉ ይላል በርክሊ፦

“እጅግ በጣም የሰለጠነና የታጠቀ 20000 የኣውሮጳ ወታደር ኣለን፡ በኛ ታላቅ ኃይል ላይ ምን ዓይነት ኣደጋ ሊደርስ ይችላል ከዚች ኋላቀር ኣገር”

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ መሪዎች በጦር ሜዳ ላይ የበላይነት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ዲፕሎማሲም በመጠቀም ከኣውሮጳ መንግስታት ጋር ግንኙነት መስርተው ነበር። ይህንን ኣስመልቶ ራስ መንገሻ ዮውሃንስ ለምሳሌ ቀደም ብለው፡ ማለትም በ28 ኦገስት 1895 ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ታላቅዋ ብሪታንያ የኢትዮጵያን ነጻነት በመደገፍ ጣልያንን መቃወም እነዳለበት በትህትና ኣሳስበዋል።

ዲፕሎማሲ ግን በግብር ስላልተተረጎመ ባራቴሪ ኃይሎቹን ኣሰባስቦ ከዕዳጋ ሓሙስ ወደ ማይ ገበጣ ከዛም ወደ ሶርያ ተራራ በ13 ፌብርዋሪ 1896 በማንቀሳቀስ ዓድዋ ላይ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰፈረበት ኣከባቢ ቦታ ያዘ።

ባራቴሪ ሶርያ ከመድረሱ ከኣንድ ቀን በፊት ጣልያኖች ያልጠበቁት ችግር ገጠማቸው። ከጎናቸው ተሰልፈው የኢትዮጵያን ሠራዊት ይወጋሉ ብለው ያመኗቸውና የጠበቋቸውን እነ ራስ ስብሓትና ደጃች ሓጎስ ጣልያንን መውጋት ጀመሩ። ስለሆነም የጣልያን ሠራዊት ተርበተበተ፡ ወሬውን የደረሳቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች ደግሞ ፈነጠዙ። ጣልያኖች በመገረም እንዲህ ብለው ተናገሩ ይባላል፦

ras Sebhat e degiac Agos, abandonano le nostre posizione e passano con sei cento uomini nel campo di Minelik

በቀጥታ ሲተረጐም "ራስ ስበሓትና ደጃች ሓጎስ የእኛን ቦታዎች እርግፍ አድርገው በመተውና ስድስት መቶ ሰዎች ከነሱ ጋር በመውሰድ ከምኒሊክ ጦር ሰፈር ጋር ተቀላቅለዋል"

በርግጥም ራስ ስብሓትና ደጃች ሓጎስ ከሌሎች የኢትዮጵያ ጀግኖች ጋር ተዋህደዋል። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ራስ ስብሓት የዓጋመ ሕዝብ በጣልያኖች ላይ እንድያምጽ ኣዋጅ አስተላለፉ። በ13ና 14 ፌብርዋሪ ደግሞ ኃይሎቻቸውን በሰዓቲ ኮረብታዎችና ዓላቛ ተራራ ላይ አሰፈሩ። ጣልያኖች ደግሞ ራስ ስበሓትን ለመውጋት በሌፍተናንቶች ቺሰተሪኒ፡ ዲኮንሲሊስ፡ ነግሬቲ ና ካፑቶ የሚመራውን ሠራዊታቸውን ከዓዲግራት ውጭ ማንቀሳቀስ ጀመሩ።

ጣልያኖች ባጣም ያሰጋቸውና "የዓጋመ አብዮት" ብለው የሰየሙትን በግዜው ዓድዋ ኣከባቢ ስለሁኔታው ዘገባ ይጽፍ የነበረውን የማንቸስተር ጋርድያን ጋዜጠኛ እንግሊዛዊ ኦገስተስ ብላንዲ ዋይልድ "የዛሬይቱ አቢሲንያ" በሚል መጽሓፉ ላይ እንዲህ ይላል፡-

"የዓጋመ ገበሬዎች እጅግ በጣም ጦር-ወዳጅ ናቸው፡ በጠመንጃ ተኵስም የሚደነቁ ናቸው። ጠመንጃ ከማግኘታቸው በፊትም በጦርና ጋሻ ፍልምያ ላይ አድናቆት ያተረፉ ናቸው"

ስለሆነም ከዓዲግራት የዘመተውን የጣልያን ሠራዊት በታተኑት፡ ከቺሰተሪኒ በስተቀረም እላይ የተጠቀሱትን ሌፍተናንቶች ከብዙ ወታደሮቻቸው ጋር ተማረኩ፡ ተገደሉ።

ጣልያኖች ግን ትዕቢት ወጥሯቸው ስለነበር፡ 'በደንቃራ በቅሎ ቃጭል ተንጠልጥሎ' እንዲሉ፡ ባራቴሪ አስፈላጊውን ጥናት ሳያደርግ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ዘመቻ ለማካሄድ ዝግጅት አደረገ።

የዓድዋ ጦርነት ማርች 1 1896

በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ፡ በፌብርዋሪ 29 ባራቴሪ አራት ብሪጌዶች በማሰለፍና ወደ ኢትዮጵያ ሠራዊት በመቅረብ ቦታ ያዘ። ቦታ እንድይዙ ትእዛዝ የተሰጣቸው አራቱ የጣልያን ብርጌዶች 1) በጀነራል ኣልበርቶኒ የሚመራው ያገር ሰዎች (ኤርትራውያን) ብርጌድ፡ 2) በጀነራል አሪሞንዲ የሚመራው የኣንደኛ እግረኛ ብሪጌድ፡ 3) በጀነራል ዳቦርሚዳ የሚመራው የሁለተኛ እግረኛ ብሪጌድ፡ 4) በጀነራል ኤለና የሚመራው የሦስተኛ እግረኛ ብሪጌድ።

በዛን ግዜ ሮበርቶ ባታልያ የተባለው ኢጣልያዊ ባሳተመው carta demonostrativa del terreno e delle truppe in movimento nella battaglia di adua 1 marzo 1896 (የመልከኣ ምድርና የወታደሮች እንቅስቃሴ በኣንድ ማርች የዓድዋ ጦርነት) እንደገለጸው የሁለቱ ሠራዊት አቀማመጥ እንዲህ ነበር፡-

የዳቦርሚዳ ብሪጌድ በቀኝ በኩል፡ የአልበርቶኒ በግራ በኩል፡ የአሪሞንዲና ኤሌና ሁለት ብሪጌዶች ደግሞ ከመሃል ተሰልፈው ነበር። ከነዚህ የጣልያን ብሪጌዶች ፊት ለፊት የኢትዮጵያ ሠራዊት ደግሞ፡ የራስ መኰንን፡ የዋግሹም ጓንጉል፡ የራስ መንገሻ ዮውሃንስ፡ ራስ አሉላና የመንገሻ አቲከም በግራ በኩል፡ ያአጼ ምንሊክ፡ የእተጌ ጣይቱ፡ የፍተውራሪ ገበየሁ፡ የንጉስ ተክለኃይማኖት ሠራዊት በቀኝ በኩል ተሰልፈው ነበር።

እነዚህ የኢትዮጵያ አርበኞች ለአንድ ኢትዮጵያና ለነጻነቷ የተባበረ ክንድ ብያሳዩም ቅሉ አሰላለፋቸው ግን በጎሳ የተመሰረተ ነበር። ለምሳሌ አጼ ምንሊክና እተጌ ጣይቱ ከሸዋ፡ ከደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኦሮሞ ወታደሮች፡ ራስ መኰንን ከሸዋና ከሃረር ሠራዊት፡ ራስ ኦሌ (ወሌ) ከወሎ አማራና ኦሮሞ ወታደሮች፡ ራስ ሚካኤል ከወሎ ኦሮሞ ሠራዊት፡ ዋግሹም ጓንጉል ከዋግና ላሰታ አማራ ወታደሮች፡ ራስ መንገሻ፡ ራስ አሉላ፡ ራስ ስብሓት፡ ደጃች ሓጎስ፡ ከትግራይ ሠራዊት፡ ንጉስ ተክለኃይማኖት ደግሞ ከጎጃም አማራ ወታደሮች።

የኢትዮጵያ ኃይል ወደ 70000 የሚገመት ሠራዊት ሲሆን፡ የጣልያን ደግሞ 17700 የወታደር ኃይል ነበረው። ኢትዮጵያውያን የአከባቢውን መልክአ ምድር በደንብ አውቀዉት ነበር፡ ጣልያኖች ግን በረኻ ውስጥ ገብተው እንደጠፉ የሆኑት። ጣልያኖች ኢትዮጵያውያን በዕለተ ሰንበት (ማርች 1 1896 ኡሁድ ነበር) አይዋጉም የሚል እምነት አሳድረው ነበር፡ ኢትዮጵያውያን ግን አስፋላጊውን ዝግጅት አድርገው በተጠንቀቅ ይጠባበቁ ነበር። በተጫማሪም ጣልያኖች የኢትዮጵያ ሠራዊት ስለእንቅስቃሴአቸው ያላወቀ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን የራስ አሉላ ሰላዮች የጣልያንን ሠራዊት እንቅስቃሴ በሚመለከት ሙሉ ዘገባ አቅርበው ስለነበር፡ ራስ አሉላ ያገኙትን የጠላትን መረጃ በሙሉ ለሌሎች የኢትዮጵያ መሪዎች አስተላልፈው ነበር።

ጦርነቱ ልክ በ6 ሰዓት ከጠዋቱ ተጀመረ። የአጼ ምንሊክ፡ ንጉስ ተክለኃይማኖት፡ ራስ ሚካኤልና ራስ መንገሻ ሠራዊት የአልበርቶኒን ብርጌድ ከበበ፡ ሙሉ በሙሉም አወደማቸው ማለት ይቻላል፡ ሌሎች የኢትዮጵያ ወታደሮች ደግሞ የአሪሞንዲን ብሪጌድ ማጥቃት ስለጀመሩ የጣልያን ወታደሮች መበታተን ጀመሩ፡ የተሳሳተ አቅጣጫም ስለመሄዳቸው አሪሞንዲና አልበርቶኒ በፍጹም አልተገናኙም። የመገናኛ ቦታ ብለው ያቀዱትን ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስትያን ደግሞ ካርታው ውስጥ በስሕተት ስላሰቀመጡት ለመበታተንና ለመጥፋታቸው ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል።

በጀነራል አልበርቶኒ ብርጌድ ውስጥ የስምንተኛው ያገር ሰዎች እግረኛ ጦር አዛዥ የነበረውን መጀር ጋመራ ስለጦርነቱ ያይን ምስክር ዘገባ ስያቀርብ፦

“25000 ወታደሮች አዲስ ማዕበል በኛው ላይ ተለቀቀ፡ ይህ ማዕበል ነው ደግሞ ያገር ሰዎች ብሪጌድን የዋጠው፡ የበታተነው፡ የደመሰሰው” ይላል።

ስለሆነም ባራቴሪ የብርጌዶቹን እንቅስቃሴ ማስተባበር አልቻለም። ሌላ ጣልያኖች ያላወቁት ምስጢር ደግሞ ከበስተጀርባ ለማጥቃት የተዘጋጀው 15000 የኢትዮጵያ ሠራዊት ማርያም ሸዊቶ ውስጥ አድፍጦ ነበር።

ከቀኑ 10:45 የኣልበርቶኒ ወታደሮች የመጨረሻ ዙርያ ተኵሳቸውን ለቀቁ፡ የጨበጣ ውግያም ተጀመረ። ከቀኑ 12 ሰዓት ወይም እኩለ ቀን ኣከባቢ የተኵስ ድምጽ ጠፋ። ተፈጸመ። 6ሺ የጣልያን ወታደሮች ሲገደሉ፡ 2ሺ ቆስሏል፡ 2ሺ ተማርኳል፡ የተቀሩት ከሦስት ሺ በላይ የሚሆኑት ደግሞ አምልጠው ወደ ኤርትራ የገቡ ኣሉ፡ ግማሹ ግን በኣካባቢው ሕዝብ እርምጃ ተጠቅቷል። ጀነራል ኣልበርቶኒ እጁን ለኢትዮጵያ ሰጠ፡ ጀነራል ኣሪሞንዲና ጀነራል ዳቦርሚዳ ተገደሉ።

ኦገስተስ ብላንዲ ዋይልድ በቀረበው ዘገባ ስለተቸነፈው የጣልያን ሠራዊት ማፈግፈግ ያወራል፦ "የምያፈግፈው የጣልያን ሠራዊት በሓበሾች እየተነዳ እስከ እንትቹ ደረሰ፡ በእጃቸውም ላይ ወደቀ፡ የተቀሩት ደግሞ በዓጋመ ሕዝብ ጥቃት ተደመሰሱ"

## የዓድወ ድልና ያስከተለው የዓለም ኣቀፍ የፖለቲካ ተጽእኖ

ከዓድዋ ድል በኋላ በዓለም ኣቀፍ ደረጃ የተፈጠረውን የፖለቲካ ሁኔታ ከማየታችን በፊት ጦርነቱ ሳይጀመር የነበረውን የጣልያን ኣመለካከትና አቋም ማየቱ ኣስፈላጊ ነው።

ቀደም ብየ እንደገለጽኩት ሁሉ ጣልያኖች በትዕቢት ተወጥረው፡ በጥቍር ሕዝብም የነበራቸውን ንቀትና ጥላቻ፡ እንዲሁም በኣፍሪቃ ቀንድ የቅኝ ግዛት ለመፍጠር ከነበራቸው ምኞት ጋር ነው ዓድዋ ጦርነት ውስጥ የተዘፈቁት። በዲፕሎማሲ መስክ ይሁን በወታደራዊ እንቅስቃሰያቸው ላይ ከፍተኛ ተምክህተኝነትን ኣሳይቷል። በኩራትና አገር ወዳድነት የተመሰረተውን የኢትዮጵያውያን ስነልቦናዊ ኣመለካከትም በፍጹም ሊረዱት አልቻሉም።

ይህንን የጣልያን ስነምግባርም ኣንቶኔሊ የተባለው የጣልያን ዲፕሎማት ከኣጼ ምንሊክና ከእቴጌ ጣይቱ ባደረገው ግኑኝነትና፡ ንጉሠ ነገሥቱና ንግሥቲቷ ባሉበት፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያቀረበውን ንግግር ከሞላ ጎደል የምያንጸባርቅ ነው። እንዲህም ይላል፦

"ኣንቀጽ 17 ኣስመልክቶ ኢጣልያ ስህተት ማድረግዋን ለሌሎች የዓለም ኃያላን ማሳወቅ የለባትም፡ ኵራትዋን መጠበቅ ኣለባትና"

እተጌ ጣይቱም መለስ ያደርጉና፡ "እኛም ለኃያላኑ፡ የተባለውን ኣንቀጽ፡ በቋንቋችን እንደተጻፈው ሁሉ፡ ሌላ ትርጉም እነዳለው ኣስታውቀናል። እኛም እንደናንተ ኩራታችንን መጠበቅ ይኖርብናል፡ ኢትዮጵያ የናንተ ጥገኛ ወይም ቅኝ ግዛት እንድትሆን ትመኛላችሁ፡ ይህ ግን ፍጹም ኣይሆንም።"

ጣልያኖች እተጌ ጣይቱን ብያዳምጡና የኢትዮጵያውያን ቆራጥነትን ከግምት ብያስገቡት ኖሮ ዓድዋ ላይ ሠራዊታቸውን ከመዓት ያድኑት ነበር። በትዕቢት ሰክረው ስለነበር ግን ኣንድ ወር ተኩል ከዓድዋ ጦርነት በፊት፡ ማለትም በጃንዋሪ

18 1896 condizione de pace ወይም ‘የሰላም ቅድመ-ሁኔታ’ ብለው ለኢትዮጵያ ያስረከቡት ሰነድ ይዘቱ ከሞላ ጎደል እንዲህ ነበር፦

1) ንጉሠ ነገሥቱና ራሶቹ የኢጣልያ ኣገዛዝ መቀበል ኣለባቸው
2) ኢጣልያ ያልፈቀዳቸውን ማንኛውም የመሬት ወይም የንግድ ኪራዮችና ፈቃዶች ለውጭ ሰዎች እንዳይደረግ
3) ኢትዮጵያ በጠቅላላ የኢጣልያ ጥገኛ (protectorate) ትሆናለች
4) የሁሉም ራሶች ሹመት በኢጣልያ ፈቃደኛነት እንዲፈጸም
5) የኢትዮጵያ ግምሩኮችና የኣምጪ ግብር በኢጣልያ እንዲተዳደር፡ የኢትዮጵያ ገንዘብም በኢጣልያ አማካኝነት እነዲታተም
6) ያለኢጣልያ ፈቃጅነት ማንኛውም የውጭእርዳታ ሰምምነት እንዳይፈረም/እንዳይፈጠር
7) የኢጣልያ ዜጎች መሬት እንዲገዙ እንዲፈቀድላቸው
8) ማንኛውም የፖለቲካ ጠብ ለመፍትሔው ወደ ሮም እንዲተላለፍ
9) ንጉሡና ራሶቹ በተጠሩ ቍጥር የኢጣልያ ግዛት በኣፍሪቃ ላይ ለመከላከል ባላቸው መንገድና ኃይል ለመቋቋም ግዴታ ይኖርባቸዋል።

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው እንኳንስ የሰላም ቅድመ-ሁኔታ የተባለውን ወይም የኢትዮጵያ ጥገኝነት ፖሊሲያቸው ልያራምዱና፡ ጣልያኖች ዓድዋ ላይ ክፉኛ ተመተው እስከ ምጽዋዕ እንድያፈገፍጉ ተገደው ነበር። መጀመርያ የችንፈትና የውርደት ጽዋን ጠጥዋት፡ ቀጥሎም በዓድዋ ኣስፈሪ ቅዠት እንዲበረግጉ ተገደዱ፡ በዲፕሎማሲ መስክም ላይ ኢጣልያና ሌሎች የኣውሮጳ ኃያላን ሳይወዱ ኣንድ ነጻ ኣገር በኣፍሪቃ ልዑላዊነት እንዲኖራት ተቀበሉ።

የዓድዋ ድል በኣፍሪቃ፡ በኣውሮጳ፡ በመካከለኛው ምስራቅ፡ በኣስያ፡ በካሪብያንና በዩናይትድ ስታይትስ ትልቅ ተጽእኖ ኣሳደረል። የድሉ ዜና ሶማልያ፡ ደቡብ ኣፍሪቃና የመን ደረሰ፡ ህዝቦችም የኢጣልያ መቸነፍ ተቀባይነት እንዳለው ኣረጋገጡ። ቅኝ ገዢዎች ደግሞ ዓድዋ በነሱ ለሚገዛው ሕዝብ ላይ የስነልቦና ድጋፍና መነሳሳትን ይፈጥራል (ያበረታታል) የሚል ስጋት ኣደረባቸው።

በዩናይትድ ስተይትስ፡ ዓድዋ ለጥቍር አመሪካኖች የተስፋ ብርሃን ምልክት ሆነ፡ በሀይቲ የኣፍሪቃ ኩራት እንደገና ኣንሰራራ፡ እንድያውም ከዓድዋ ድል በኋላ በ1897 በኒቶ ሲልቨያን የተባለ የሀይቲ መሪ ኢትዮጵያ ድረስ በመሄድ ለኣጼ ምንሊክና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ‘እንኳን ደስ ኣላችሁ’ በማለት ድጋፉን ገልጿል።

በኢጣልያ ዋና ዋና ከተሞችና በፓርላማው ውስጥ ትልቅ የፖለቲካ ቀውስ ተፈጠረ። በዓለም ደረጃ ዝነኛ የሆኑትን ጋዜጦች እንደ ታይምስ ኦፍ ለንደን፡ ሺካጎ አሶሴትድ ፕረስ፡ ዋሽንግቶን ፖስትና ኒው ዮርክ ታይምስ ስለዓድዋ ጦርነትና ያስከተለው ተጽዕኖ ጽፈዋል።

ኒው ዮርክ ታይምስ በማርች 7 1896 እትሙ ላይ ስለ ዓድዋ ያቀረበው ዘገባ በኢትዮጵያ ድል ወይም በጣልያን ችንፈት ምክንያት ኢጣልያ ውስጥ የተከሰተውን የፖለቲካ ቀውስ በእንዲህ ያስቀምጠዋል፦

- ተቃዋሚ ሰላማዊ ሰልፈኞች መስኮቶች በመስበርና ከፖሊስና ወታደር ጋር በመጋጨት ቅሬታቸውን ገለጹ
- አክራሪ አድመኞችና ሾሻሊስቶች ዕድሜ ለምንሊክ ብለው ጮሁ
- የቀኝ ክንፍ አባላት የኢጣልያ ወታደሮች ከቅኝ ግዛቱ (ከኤርትራ) እንዲወጡ ጠየቁ
- የምክር ቤቱ ሾሻሊስቶች የኢጣልያ ወታደሮች ከአቢስንያ እንዲመለሱ በጽሑፍ ጥያቄያቸውን አቀረቡ፡ ፯ሪነታቸው ሲስልያ የሆነውን አባሎቻቸው ደግሞ አድማ ነሱ
- ፒዛ ላይ ተማሪዎች "ክሪስፒ ይውረድ፡ ወታደሮቻችን መልሱልን" የሚሉ መፈክሮች አንግበው ሰልፍ አደረጉ። ትሪቡና ና ናስዮነ የተሰኙትን የመንግስት ጋዜጦችም አቃጠሉ።

ይኸው የኒው ዮርክ ታይምስ እትም በተጨማሪ የጣልያን ወታደሮች ሁኔታ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ያቀረበው ዘገባ ርእሱ 'ወታደሮች በዓዲግራት ወጥመድ ውስጥ' ሆኖ ባጭሩ እንዲህ ያነባል፦

"ደይሊ ኒውስ ነገ ከሮም በምያስተላልፈው ዘገባ ላይ 2000 የጣልያን ወታደሮች ከግድያውና ጭፍጨፋው አምልጠው ዓዲግራት ከገቡ በኋላ በሓበሻ ሠራዊት ተከበዋል፡ የጣልያኖቹ ሁኔታ በጣም አስጊ ነው፡ በከተማይቱ ለሦስት ቀን ብቻ የሚበቃ ምግብና ውኃ ነው ያለው"

የኒው ዮርክ ታይምስ በማርች 8 1896 እትሙ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ድል እንዴት የአውሮጳን ፖሊተካ እንደቀያየረው ያትታል፦

"የኢጣልያ አሳዛኝ ውርጅብኝ አሁን ከነጭራሹ ሚዛን እንድታጠፋ አድጓታል። የዓድዋ ጦርነት አልፐስ ተራሮች ላይ ቢካሄድ ኖሮ የባሰ ምስቅልቅልና የዲፕሎማሲ ሽብርን ይፈጥር ነበር። ኢጣልያ በወረዳት ሽብር ጐረቤቶችዋም ተንቀጠቀጡ። የፈለገውን ይሁን ግን አንድ ነገር ግልጽ ነው፡ ክሪስፒ ሊመለስ አይችልም፡ ሮም ውስጥ የሚገኙት ጤናማ ተቺዎች ክሪስፒን የሚተካው ሊኖር አይችልም፡ ከምንሊክ ጋር የእርቅ ድርድር ከመፍጠርና የኢጣልያ ኃይሎች ወደ ቀይ ባሕር መውሰድና ማከማቸት ካልሆነ በስተቀረ። ንጉሥ ኡምቤርቶ ግን እንዲህ ያለ አስተሳሰብ ከመቀበል ስልጣኑን ማስረከብ እንደሚበጀው አስታወቀ።"

የጀርመን ጋዜጦች በአንጻሩ፡ የጀርመን የውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት በመወከል "ኢጣልያ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ሳታመነታ ኃይሎችዋን እጥፍ በማድረግ አሁን የወረደባትን ውርደት ለማጥፋት ማንኛውም አደጋ በመቀበል አቢስንያን መያዝ አለባት" ይላሉ።

ኢጣልያ ግን እንኳንስ የጀርመን ምክር ሰምታ ኢትዮጵያን እንደገና ለመያዝ መመኮርዋ፡ በኣንጻሩ ማርች 10 1896 ኒው ዮርክ ታይምስ እንደገለጸው ሁሉ “የጣልያን ኦፊስያላዊ ዘገባዎች ያረጋገጡት ነገር ቢኖር በኣብሲኒያ ውስጥ የደረሰው ጥፋትን አስከትሎ ከከሰላ ሳይቀር ሙሉ በሙሉ መውጣት ነው” ይላል።

የ19ኛው ክፍለዘመን ሲገባበደድ ዓድዋ ያለምንም ጥርጥር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ማስመዝገቡን ታሪክ መስክሮታል። ስለሆነም ኢትዮጵያ ብቻዋን (ከላይበርያ በስተቀረ) በጥቍር ኣፍሪቃ ልዑላዊነትዋን ኣስከብራ፡ ነጻነትዋን ተቀዳጅታ ኖራለች። የኢትዮጵያን ነጻነት ያስመሰከረው የተባባረው የኢትዮጵያ ጀግኖች ክንድ፡ ኢትዮጵያ በይበልጥ ኣንድ ሕብረ-ብሔር እንድትሆን ኣድርጓታል።

የዓድዋ ድል ግን የኢትዮጵያውያን ድል ብቻ ኣይደለም፡ ሰፋ ባለ መልኩና ታሪካዊ ይዘቱ ከታየ የዓድዋ ድል የኣፍሪቃ ሕዝብ ድል ነው፡ የጥቁር ሕዝብ ኩራት ነው፡ የጭቁን ሕዝብ መከታ ነው፡ የምዝብር ሕዝብ ተስፋ ነው፡ ለፍትሕ ለቆመ ማንኛውም ሕብረተሰብ ደግሞ ህያው ምስክር ነው፡ ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን የዓድዋ 107ኛ ዓመት የድል መታሰብያ ቀን ስናከብር ኩራት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ልዑላዊነት በመጠበቅ ለመጪው ትውልድ ይህንን ቅርጽ ማስተላለፍ ታሪካዊ ሓላፊነታችን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

አመሰግናለሁ!!